# ኪ ዳ ና ች ን
# KIDANACH'N

ልዩ ዕትም
Special Edition

መስከረም ፩ ቀን፥ ፲፱፻፺፱ ዓ. ም.
Meskerem 1, 1999 A.D
(September 11, 2006)

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥**
**ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳትና**
**የ"ኢትዮጵያ" እና "የኢትዮጵያውያን" የኾነውንም ዅሉ ለመጠበቅ፥ ለማሳወቅም፡**
**በ"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት" እየተዘጋጀ የሚወጣ ዕትም፡፡**

**Published by "Ethiopia: The Kingdom of God Services"**
**to reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God**
**and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God;**
**and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.**

# የ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት
# ቀን መቁጠሪያ
## 1999 (2006-2007) Calendar

አዘጋጅ፡- ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ

## ስለቀን መቁጠሪያው መግለጫ

፩ኛ፡ ይህ የቀን መቍጠሪያ የተዘጋጀው፡ “ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!” በሚለው፡ በ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. በታተመው መጽሓፍ ውስጥ የተገለጹትንና አግባብነት ያላቸውን ሓተታዎች መሠረት በማድረግ ነው።

፪ኛ፡ “በዘንዜከር” በተባለው፡ የየዕለቱ፡ የጸሎት መግቢያ፡ ለመዓልቱና ለሌሊቱ ቅመራ፡ መነሻ ኾኖ፡ ከሌሎቹ ቁጥሮች ጋር የሚደመረው፡ የ፲፱፻፺፱ ዓ. ም. ዓበቅቴ፡ ፲፪ (አሥራ ኹለት)÷ መጥቅዑ ፲፰ (አሥራ ስምንት) መኾኑ ይታወቅ!

፫ኛ፡ በቀን መቁጠሪያው ሠንጠረዥ ውስጥ፡ በስም ብቻ የተጠቀሱት ጻድቃን፡ ዕረፍታቸውን÷ የአኀዞች የተለያዩት ቀለማት ደግሞ፡ የሚከተሉትን አብነቶች ያመለክታሉ። (ሀ) ቀዩ፡ ሰንበተ ክርስቲያንን÷ ዓበይት በዓላትንና ተከታታዮቹን የደስታ ዕለታት÷ (ለ) አረንጓዴው፡ ቀዳሚት ሰንበትን እና ንዑሳን በዓላትን÷ (ሐ) ሓምራዊው፡ የሰባቱን አጽዋማት ቀኖች፡ ረቡዕንና ዓርብን ጭምር ያሳያሉ።

፬ኛ፡ መስከረም ፩ ቀን፡ አሮጌ የኾነውን ኹሉ ጥለን÷ ከየኹለንተናችን፡ በንስሓ አስወግደንና በመንፈስ ቅዱስ ታድሰን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም በመወለዱ፡ የተገኘውን ዘለዓለማዊውን የምሕረት ዘመን÷ የክብር ልብስና የሕይወት አክሊል፡ እንደአዲስ ተሸላሚ ተቀብለን የምንጌናጸፍባትና የምንቀዳጅባት ዕለት ስለኾነች÷ ከዚህም ጋር፡ ለጌታችንና ለእመቤታችን የልደት በዓላት አክብሮት፡ ሥጋችንንና ነፍሳችንን÷ መንፈሳችንንም፡ በሥጋ ወደሙ ቀድሰን ለማብቃት፡ ከአሮጌው፡ ወደአዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባትን ጻጉሜን፡ እንደጾመ ገሃድና ንዑስ ሱባዔ አድርገን፡ በጸሎት እናሳልፋታለን።

## ስለቀን መቁጠሪያው ልዩ ማሳሰቢያ

ለየወሩ፡ ምንባቦች ተመድበዋል። እነዚህም የተዘጋጁት፡ በሳምንቱ የሥራ ቀኖች፡ በየዕለቱ፡ ለጧትና ለማታ፡ እጅግ ቢያንስ፡ ኹለት ምዕራፎችን÷ እንዲሁም፡ በየሳምንቱ የቅዳሜና እሑድ ዕለታት÷ በሌሎቹም የበዓላትና የዕረፍት ጊዜያት፡ በተቻለ መጠን፡ ምዕራፎቹን ጨማምሮ በማንበብ ለመጨረስ እንደሚቻል በመገመት ነው። ምንባቡ፡ በግል÷ ወይም በኅብረትና በቤተሰብ ተሰባስበው ሊካኼድ ይቻላል። መዝሙረ ዳዊት፡ በየቀኑ፡ በጸሎት መልክ ስለሚደገም፡ በምንባቡ ውስጥ አልታከለም።

ይህን የቀን መቍጠሪያ÷ ደግሞም፡ በቅርቡ÷ “ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት” በሚል፡ አዲስ ተከታታይ ርእስ ሥር፡ “አንደኛ መጽሓፍ”÷ “ኹለተኛ መጽሓፍ” እና “ሦስተኛ መጽሓፍ” ተብለው÷ እንዲሁም፡ ቀደም ብለው፡ “ኢትዮጵያዊው÷ በማንነቱ ፍለጋ!”÷ “ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!” እና **Ethiopia: The Classic Case** በሚሉ አርእስት፡ ታትመው የወጡትንና እየተሠራጩ ያሉትን÷ ሌሎችንም፡ ወደፊት እየታተሙ የሚወጡትን ዕትሞችና መጻሕፍት ለማግኘት፡ ከዚህ በታች በተመለከቱት፡ ባሳታሚው አድራሻዎችና የመገናኛ መስመሮች፡ መጠየቅና መጠቀም ይቻላል።

---


አሳታሚ እና አከፋፋይ
Publisher & Distributor
**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።**
**Ethiopia: The Kingdom of God Services**
መልእክት ሣጥን ቁጥር 8)02 — P. O. Box 812
ስልክና ዕምነቅ ቁ. 06-08- * 5 እና @-00- * 5 — Tel. & Fax. 16-18-85 & 20-00-85
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ። — Addis Abeba, ETHIOPIA
ወይም — or
**P. O. Box 43262 ~ Washington, DC 20010-9262 ~ USA.**
**Tel.: 301-587-8074 ~ Fax.: 301-587-1971**
Email: ekogyesus@aol.com
Web Site: www.ethkogserv.org


---

# ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ወርኀ መስከረም ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

1999 Era of Mercy. Month of Meskerem (Sept.-Oct., 2006). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፩ የኢየሱስ ክርስቶስ እና የድንግል ማርያም ልደታት፤ የኢትዮጵያ ነጻነት፤ ኪዳነ አዳምና ሔዋን፤ ራጉኤል ሊቀ መላእክት፤ በርተሎሜዎስ ከ02ቱ ሓዋርያት 1ዱ:: 11 | ፪ 12<br>ዮሐንስ መጥምቅ | ፫ 13<br>አባ አንበስ ኢትዮጵያዊ | ፬ 14 | ፭ 15<br>በሄሮድስ የተፈጁት ሕፃናት፤ አጼ ንብለ ድንግል፡ የአሕመድ ግራኝን ወረራ፡ በአገር ፍቅርና በሃይማኖት ጽናት ተቋቁሞ የተጋደለ | ፮ 16<br>ኢሳይያስ ነቢይ |
| ፯ ኢትዮጵያዊቷ ኤልሣቤጥ፡ የመጥምቁ ዮሓንስ እናት:: መናኔ መንግሥት አጼ ተክለ ሃይማኖት ለሥልጣን መጋደሉን ጠልቶ፡ ወደገዳም የገባ:: 17 | ፰ 18<br>ግዝረተ ኢየሱስ | ፱ 19 | ፲ 20<br>አጼ መስቀል ግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ የገባበት | ፲፩ 21<br>አጼ በካፋ፡ ስመ ጥሩው ምሁር መሪ | ፲፪ 22<br>ስለንስጥሮስ ኑፋቄ የ2) ሊቃውንት ጉባኤ በኤፌሶን | ፲፫ 23 |
| ፲፬ 24 | ፲፭ 25 | ፲፮ 26<br>ኪዳነ ኖኅ:: ደመራ፡ (በመስቀል ዋዜማ ማታ፡ በችቦ እሳት ለሚነደው ቋሚ፡ ለጋ ዛፍ እያመጡ መደመር) | ፲፯<br>ኢየሱስ ክርስቶስ የተሠዋበት እውነተኛ መስቀል የተገኘበት 27 | ፲፰ 28<br>አባ ኤዎስጣቴዎስ ኢትዮጵያዊ፡ ስለቅዳሜ፡ ቀዳሜ ሰንበትነት የተከራከረ | ፲፱ 29 | ፳ 30 |
| ፳፩ 1<br>የቅድስት ድንግል ማርያም ዕርገት፤ የልጇም መስቀል ዜና የሚነገርበት:: | ፳፪ 2 | ፳፫ 3 | ፳፬<br>ኪዳነ መልከ ጼዴቅ 4 | ፳፭<br>ዮናስ ነቢይ፤ የክረምት ወራት ማብቂያ 5 | ፳፮ 6<br>የጽጌ ወራትና የሕፃኑ ኢየሱስና የቅድስት እናቱ የስደት ጾም መግቢያ | ፳፯ 7 |
| ፳፰ 8<br>ኪዳነ አብርሃም፤ የጽጌ ማኀሌት | ፳፱ 9 | ፴ 10 | ማስታወሻ:- | | | |

*"ወንዝም፡ ገነትን ያጠጣ ዘንድ፡ ከዔዶም እየወጣ ይፈስስ ነበር፤ ከዚያም ለአራት ወገን ይከፈል ነበር:: ...የወንዙ ኹለተኛ ወገን ስም፡ ግዮን ነው፤ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ኹሉ ይከብባል:: ...እግዚአብሔር አምላክም፡ ሰውን ወስዶ፡ ያበጀትም፥ ይጠብቃትም ዘንድ፡ በዔዶም ገነት አኖረው::"* ዘፍጥ. ፪፥ ፰-፲፯::

| | |
|---|---|
| የመስከረም ወር ምንባብ: | አሪት ዘፍጥረትና አሪት ዘፀአት:: |

# ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ጥቅምት ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

1999 Era of Mercy. Month of Tt'q'mt (Oct.-Nov., 2006). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | ፩ 11 | ፪ 12<br>አባ ሕርያቆስ: የቅዳሴ ማርያም ደራሲ | ፫ 13 | ፬ 14<br>አብርሃ ወአጽብሓ: ክርስትናን በኢትዮጵያ ያስፋፉ ወንድማማች ነገሥት |
| ፭ 15<br>የጽጌ ማኅሌት | ፮ 16<br>ሓና ነቢይት የሳሙኤል እናት፤ አባ ጳንጠሌዎን: ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ፤ | ፯ 17 | ፰ 18 | ፱ አጼ ዳዊት: የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል ከኢየሩሳሌም ያስመጣና 'ዓባይን እገድባለሁ' እያለ: በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ክርስቲያኖችን: ከእስላሞች ጥቃት ያዳነ:: 19 | ፲ ኢየሱስ ክርስቶስ በ፵ ቀኑ በእናቱ እቅፍ ቤተ መቅደስ የገባበት፤ በዓለ ስምዖን፤ ሓና ነቢይት፤ አጼ ፋሲል ካቶሊክነትን ተቋቁሞ: ተዋሕዶ ሃይማኖትን ያጸና:: 20 | ፲፩ 21 |
| ፲፪ 22<br>ወንጌላዊው ማቴዎስ: ከ02ቱ ሓዋርያት 1ዱ፤ ቅዱስ ድሜጥሮስ: የቀንና የዘመን አቈጣጠርን ያስተካከለ፤ የጽጌ ማኅሌት | ፲፫ 23 | ፲፬ 24<br>ኢትዮጵያዊዉን ጃንደረባ አቤሜሌክን ያጠመቀው ፊልጶስ ሓዋርያ፤ አባ ዘሚካኤል አቡነ አረጋዊ: ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ፤ ገብረ ክርስቶስ፤ | ፲፭ 25 | ፲፮ 26 | ፲፯ 27<br>እስጢፋኖስ: ቀዳሚው ሰማዕት: የሹመቱ መታሰቢያ:: ዲዮስቆሮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘግብፅ: የተዋሕዶ ሃይማኖት ተጋዳይ:: | ፲፰ 28 |
| ፲፱ 29<br>የመጀመሪያዎቹን እስላሞች ስደተኞች በኢትዮጵያ አስተናግዶ የሸኘው ክርስቲያኑ አጼ ይምራሕ፤ የጽጌ ማኅሌት | ፳ 30 | ፳፩ 31 | ፳፪ 1<br>ወንጌላዊው ሉቃስ | ፳፫ 2 | ፳፬ 3 | ፳፭ 4 |
| ፳፮ 5<br>የጽጌ ማኅሌት | ፳፯ 6 | ፳፰ 7<br>አማኑኤል፤ አባ ይምዓታ: ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ፤ | ፳፱ 8 | ፴ 9 | ማስታወሻ:- | |

*"እግዚአብሔር: ኖኅን አለው:-'የፈጠርሁትን ፍጥረት ኹሉ: ከሰው እስከእንስሳ፥ ከተንቀሳቃሽ እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ: ከምድር ገጽ አጠፋለሁና: አንተ: ቤተሰቦችህን ኹሉ ይዘህ: ወደመርከብ ግባ! በዚህ ትውልድ መካከል: በፊቴ: የእውነት ሰው ኾነህ አግኝቼሃለሁና!' ኖኅም: እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ::...እግዚአብሔርም: በስተኋላው ዘጋበት:: የጥፋት ውኃም: በምድር ላይ: አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ዘነበ፤ ውኃውም በዛ፤ መርከቢቱንም አነሣ፤ እርሷም: በውኃው ላይ ተንሳፈፈች!"* የጥምቀት ምሳሌ ለኾነው: ለመጀመሪያው ሃይማኖታዊ ጉዞ: ቀይ ባሕርን አቋርጣ: አራራት ላይ ለማረፍ: ከኢትዮጵያ ተነሣች:: ዘፍጥ. ፯፥፩-፲፯::

| የጥቅምት ወር ምንባብ: | መጽሓፈ ሳሙኤል፥ መኃልየ ሰሎሞን:: |
|---|---|

# ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ኅዳር ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

1999 Era of Mercy. Month of H'dar (Nov.-Dec., 2006). Year of` Luke the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ቅዳሜ Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | | ፩ 10 አጼ ነአኵቶለአብ መንግሥቱን: በኢትዮጵያዊው የመልከ ጼዴቅ ሥርዓት የመራና ያስተዳደረ:: | ፪ 11 |
| ፫ 12 የማኅሌተ ጽጌ ፍጻሜ | ፬ 13 | ፭ 14 ለንጊኖስ: የተሰቀለ ጌታን: ጎኑን በጦር የወጋና ኋላ አምኖ: በሰማዕ ትነት የተጋደለ | ፮ 15 ቊስቋም፤ የሕፃኑ ኢየሱስና እናቱ ስደት በዓል<br><br>የጽጌ ጾም ፍጻሜ | ፯ 16 | ፰ 17 አርባዕቱ እንስሳ: የእግዚአብሔርን መንበር የሚሸከሙ | ፱ 18 ስለአርዮስ ኑፋቄ የ3)08 ሊቃውንት ጉባኤ በኒቅያ |
| ፲ 19 | ፲፩ 20 ቅድስት ሐና ኢትዮጵያዊት: የድንግል ማርያም እናት | ፲፪ 21 ሚካኤል ሊቀ መላእክት፤ አጼ በእደ ማርያም: ሃይማኖታዊው ተጋዳይ | ፲፫ 22 አእላፍ መላእክት | ፲፬ 23 በ09)^7 ዓ. ም. በደርግ የዓመፅና የክህደት ዘመን: የኢትዮጵያውያን እልቂት መነሻ | ፲፭ 24 | ፲፮ 25 የጾመ ነቢያት መግቢያ |
| ፲፯ 26 አዲስ አበባ በ08)&9 ዓ.ም. የተቈረቈረችበት | ፲፰ 27 ፊልጶስ: ከ02ቱ ሓዋርያት 1ዱ | ፲፱ 28 | ፳ 29 | ፳፩ 30 ኪዳነ ሙሴ፤ ማርያም ጽዮን፤ ማክዳ ንግሥትና ልጇ ምኒልክ | ፳፪ 1 | ፳፫ 2 ቆርነሌዎስ ጻድቅ (የሓዋ. ምዕ. 0) |
| ፳፬ 3 | ፳፭ 4 መርቆሬዎስ ሰማዕት | ፳፮ 5 "4ቱ ካህናተ ሰማይ፤ በናግራን (የመን) የኢትዮ ጵያውያን ሰማዕ ታት፤ የአጼ ካሌብ ድል፤ ኢየ ሱስ ሞዐ ዘሓይቅ | ፳፯ 6 አባ ሊቃኖስ ኢትዮጵያዊ ዘደብረ ቊንጽል | ፳፰ 7 አባ ሊቃኖስ: ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ | ፳፱ 8 የሊቀ ሓዋርያት ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር ቀሌምንጦስና ተፍጻሜተ ሰማዕት ሊቀ ጳጳሳት ጴጥሮስ | ፴ አጼ ገብረመስቀል፤ በዘመኑ: የቅዱስ ያሬድ ሙያና የ9ቱ ቅዱሳን ዜና የገነነበት፤ የጾመ ነቢያት ማብቂያ 9 |

*“...የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የኾነው መልከ ጼዴቅ: የኅብስተ አኰቴትና የጽዋዓ በረከት ቊርባንን አዘጋጅቶ: አብራም: ጠላቶቹን ነገሥታት ወግቶ ሲመለስ: 'አብራም: ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ: ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው' ብሎ ባረከው፤ አብራምም: ከኹሉ ሀብቱ: አሥራትን: ለመልከ ጼዴቅ ሰጠው::” የእሥራኤላውያን አባት የኾነውን: አብርሃምን: ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያበቃው: የኢትዮጵያ ውያን አባት የኾነው: የኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ ቡራኬ መኾኑን ማስተዋል ነው:: ዘፍጥ. ፲፬÷ ፲፯-፳::*

| የኅዳር ወር ምንባብ: | ትንቢተ ኤርምያስና ትንቢተ ሕዝቅኤል:: |
|---|---|

# ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ታኅሣሥ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

1999 Era of Mercy. Month of Tah'sas (Dec., 2006-Jan, 2007). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሐሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 10<br>ዕለተ ትስብእት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የተፀነሰበት፤ ብሥራተ ገብር ኤል፤ ኤልያስ ነቢይ፤ ቤትሳባ ኢትዮጵያዊት፡ የሰሎሞን እናት፤ የጾመ ማርያም መግቢያ | ፪ 11 | ፫ 12<br>ሕጻን ማርያም በስዕለት ለቤተ መቅደስ የተሰጠ ችበት፤ ፋኑኤል ሊቀ መላእክት፤ ዳግማዊ አጼ ምኒ ልክ፤ ሀብተ ጊዮ ርጊስ አባ መላ | ፬ 13<br>እንድርያስ፡ ከ02ቱ ሓዋርያት 1ዱ | ፭ 14 | ፮ 15<br>በ09)#3 ዓ. ም. በፋሺስት ጣልያን፡ በሰማዕትነት የተሰየፉት የአዲስ ዓለም ማርያም ካህናት | ፯ 16<br>ፅንሰታ፡ ድንግል ማርያም የተፀነሰችበት |
| ፰ 17<br>ስብከት፤<br>ኢትዮጵያዊው አባ ኪሮስ | ፱ 18<br>አባ በአሚን ኢትዮጵያዊ | ፲ 19<br>በወሎ፡ ደብረ እግዚአብሔርና የሓይቅ መካነ እስጢፋኖስ፡ በኣሕመድ ግራኝ ጦር የተበዘበዙበት | ፲፩ 20 | ፲፪ 21<br>ኢትዮጵያዊው አባ ሳሙኤል፡ የዋልድባው | ፲፫ 22 | ፲፬ 23<br>በ09)@8 ዓ.ም. የፋሺስት ጣል ያን አየር ኃይል በኢትዮጵያ ላይ የመርዝ ጢስን ማዝነብ የጀመረበት |
| ፲፭ 24<br>ብርሃን | ፲፮ 25 | ፲፯ 26 | ፲፰ 27<br>በሊቀ ካህናት እንበረም ተልኮ ጵጵስናን የተሾመ አባ ሰላማ ኢትዮጵያዊ | ፲፱ 28<br>ቅዱስ ገብርኤል፡ ፫ቱ ደቂቅን ከባቢሎን እሳት ያዳነበት | ፳ 29 | ፳፩ 30 |
| ፳፪ 31<br>ኖላዊ | ፳፫ 1<br>ኪዳነ ዳዊት | ፳፬ 2<br>የእቲሳው እጨጌ ተክለ ሃይማኖት ልደት | ፳፭ 3<br>የጽጌ ወራት ማብቂያ | ፳፮ 4<br>የበጋ ወራት መግቢያ | ፳፯ 5<br>አጼ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ | ፳፰ 6<br>አማኑኤል |
| ፳፱ 7<br>በዓለ ወልድ | ፴ 8 | ማስታወሻ:- | | | | |

*ኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ ከባረከው በኋላ፡ እግዚአብሔር ተገልጦለት፡ "እኔ ኤልሻዳይ ነኝ! በፊቴ ተመላለስ! ፍጹምም ኹን! ቃል ኪዳኔን፡ በእኔና በአንተ መካከል አደርጋለሁ! እጅግም አበዛሃለሁ! ...ከዛሬ ጀምሮም፡ እንግዴህ፡ ስምህ 'አብራም' ተብሎ አይጠራ! ነገር ግን ስምህ፡ 'አብርሃም' ይኾናል፤ ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና!" ያለው፡ ይህ የሃይማኖትና የምግባር ሰው፡ ከተገረዘና ሣራ ከሞተች በኋላ፡ ኢትዮጵያዊቷን ኬጡራን፡ በሚስትነት አግብቶ፡ ልጆችን መውለዱ፡ ለኢትዮጵያዊነት አንጻ አብነት ኾኗል፡፡ ዘፍጥ. ፲፯፤ ፳፫፤ ፳፭፡፡*

| የታኅሣሥ ወር ምንባብ፡ | ትንቢተ ኢሳይያስና ትንቢተ ዳንኤል፡፡ |
|---|---|

# ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ጥር ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

1999 Era of Mercy. Month of Tt'rr (Jan.-Feb., 2007). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | ፩ 9<br>እስጢፋኖስ:<br>እንደጌታው:<br>ለእውነት በይፋ<br>መስክሮ የተሠዋ<br>ቀናዒ ዲያቆንና<br>ቀዳሜ ሰማዕት | ፪ 10<br>አቤል ጻድቅ | ፫ 11<br>አባ መጣዕ<br>(ሊባኖስ)<br>ኢትዮጵያዊ | ፬ 12<br>ወንጌላዊው<br>ዮሓንስ: ከ02ቱ<br>ሓዋርያት 1ዱ | ፭ 13 |
| ፮ 14<br>ኖኅ፤<br>ዕርገተ ኤልያስ | ፯ 15<br>የአስተርእዮ<br>ቅድስት ሥላሴ<br>(የጥር ሥላሴ) | ፰ 16 | ፱ 17 | ፲ 18<br>ከተራ:<br>(በበዓሉ ዋዜማ:<br>ለጥምቀት<br>የሚኾን ውኃ:<br>ከወንዝ ተወስዶ<br>የሚከተርበት)፤<br>ጾመ ማርያምን<br>ለማይጾም:<br>ጾመ ገሃድ | ፲፩ 19<br>በዓለ አስተርእዮ<br>ወጥምቀት::<br>ኢትዮጵያዊው ጃንደ<br>ረባ አቤሜሌክ:: በቅ<br>ዳሴ ጸሎቱ: የጥምቀ<br>ት ወንዝ የቆመለት:<br>የተጕለቱ ታቦት ዋሻ<br>ካህን: ትልቁ ወልደ<br>ኢየሱስ | ፲፪ 20<br>ጌታ:<br>በቃና ዘገሊላ<br>ሠርግ: በቅድስት<br>እናቱ ፈቃድ:<br>የመጀመሪያ<br>ተአምሩን<br>ያሳየበት፤<br>ሊቀ መላእክት<br>ሚካኤል |
| ፲፫ 21<br>መርዓዊ፤<br>በ#4 ዓ.ም. በዘ<br>መኗ: በጃንደረባዋ<br>አማካይነት: ክርስ<br>ትና ወደአገርዋ<br>የመጣላት<br>ሕንደኬ<br>ንግሥተ<br>ኢትዮጵያ | ፲፬ 22<br>እንበረም: ሊቀ<br>ካህናት ዘአኵስም:<br>በ3) "5 ዓ.ም.<br>ሥርዓተ<br>ቤተ ክርስቲያንን<br>ወደኢትዮጵያ<br>ያስመጣ | ፲፭ 23<br>ቂርቆስ:<br>የ፲ ዓመት ሕጻን<br>ሰማዕት | ፲፮ 24<br>ኢየሉጣ ሰማዒት:<br>የሕጻኑ ቂርቆስ<br>እናት | ፲፯ 25 | ፲፰ 26 | ፲፱ 27 |
| ፳ 28 | ፳፩ 29<br>የቅድስት ድንግል<br>ማርያም ዕረፍት፤<br>የጾመ ኢትዮጵያ<br>(ነነዌ) መግቢያ፤ | ፳፪ 30 | ፳፫ 31<br>የጾመ ኢትዮጵያ<br>ማብቂያ፤ | ፳፬ 1 | ፳፭ 2 | ፳፮ 3 |
| ፳፯ 4<br>ዕርገተ ኄኖክ | ፳፰ 5 | ፳፱ 6 | ፴ 7 | ማስታወሻ:- | | |

*ሙሴ: ከግብጽ ወደኢትዮጵያ መጥቶ: የኢትዮጵያዊውን ካህን: የዮቶርን ሴት ልጅ: ሲጳራን አገባ፤ የአማቱን በጎች ሲጠብቅ ሣለም: እነሆ: እግዚአብሔር ተገልጾለት: ያዘዘውን ኹሉ በመፈጸሙ: ኢትዮጵያዊነትን መቀበሉ: እውን ኾኗል:: ከዚህ ኢትዮጵያዊነቱ የተነሣም: የኋላ ኋላ: በወንድሙና በእኅቱ ሳይቀር በደል እንደደረሰበት ተጽፏል:: ሙሴና የእስራኤል ሕዝብ: ገና በምድረ በዳ ሠፍረው ሣሉ: የሚቃጠልንና ሌላ መሥዋዕትን: ለእግዚአብሔር በማቅረብ: ሥርዓተ ክህነትን÷ ስለሕዝብ አስተዳደርና ፍትሕ አሰጣጥም በማስተማር ሥርዓተ ንግሥትን: አማቱ ዮቶር: ለሙሴና ለአሮን÷ ለሕዝቡ ሽማግሌዎችም ኹሉ ማሳየቱ: ተመዝግቧል::*

*ዘጸአ. ፫÷ ፩-፭፤ ፲፰÷ ፩-፳፯:: ዘኍል. ፲፪÷ ፩-፲፭::*

| የጥር ወር ምንባብ: | መጽሓፈ ሩትና የማቴዎስ ወንጌል:: |
|---|---|

## ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ወርኀ የካቲት ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

1999 Era of Mercy. Month of Yekatit (Feb.-Mar., 2007). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡- | | | | ፩ 8<br>ስለመቅዶንዮስ ኑፋቄ የ)%<br>ሊቃውንት ጉባኤ በቊስጥንጥንያ | ፪ 9 | ፫ 10<br>የግሼን ማርያም አምባ፡ በ05)#2 ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ጦር የተመዘበረበት |
| ፬ 11<br>ዘዘወረደ (ቅበላ)<br>ጣይቱ ብጡል፡ ብርሃን ዘኢትዮጵያ | ፭ 12<br>የጾመ ሕርቃልና የዓቢይ ጾም መግቢያ፤ | ፮ 13<br>ማርያም እንተዕፍረት፡ ጌታን በሽቱና በእንባዋ እግሩን ያጠበችው | ፯ 14 | ፰ 15 | ፱ 16 | ፲ 17<br>ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ፡ ከ02ቱ ሓዋርያት 1ዱ |
| ፲፩ 18<br>ቅድስት | ፲፪ 19<br>የጌታ የ፵ ቀን ጾም መነሻ፤<br>በ09)@9 ዓ. ም. የኢትዮጵያውያን ሰማዕታት የግፍ እልቂት፡ በፋሺስት ጣልያን | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22 | ፲፮ 23<br>ኪዳነ ምሕረት፡ በድንግል ማርያም እና በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘው | ፲፯ 24 |
| ፲፰ 25<br>ምኲራብ፤<br>አዝማች ደገልሓን፡ የአሕመድ ግራኝን ወራሪ ጦር የተዋጋ ኢትዮጵያዊ ጀግና | ፲፱ 26 | ፳ 27 | ፳፩ 28<br>ከይሁዲቷ ጉዲት አገዛዝ በኋላ፡ በ9)#3 ዓ. ም. የአገዉ (ዘአገው) መርሓ ተክለ ሃይማኖት የተተካበት | ፳፪ 1 | ፳፫ 2<br>ኢትዮጵያ፡ ኃይሏ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ የተረጋገጠበት የአድዋ ድል | ፳፬ 3 |
| ፳፭ 4<br>መጻጒዕ | ፳፮ 5 | ፳፯ 6<br>አሕመድ ግራኝ በ05)#5 ዓ.ም. ድል የተመታበት | ፳፰ 7 | ፳፱ 8 | ፴ 9 | ማስታወሻ፡- |

*"ይሁዳ፡ የአንበሳ ደቦል ነው፤ ያስነሣውስ ዘንድ ማን ይችላል? ገዥ የኾነው እስኪመጣ ድረስ፡ በትረ መንግሥት ከይሁዳ፥ የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል አይጠፋም፡፡ የአሕዛብም መታዘዝ ለእርሱ ይኾናል፡፡"*
*"በዙፋኑም ላይ በተቀመጠው፡ በቀኝ እጁ ያለውን መጽሐፍ ሊዘረጋ ወይም ሊመለከተው የሚገባው ማንም ስላልተገኘ፡ እጅግ አለቀስሁ፡፡ ከሃያ አራቱ አለቆች አንዱ፡ 'ኢትብኪ! ናሁ ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ'፡ ማለትም፡ 'አታልቅስ! እነሆ፥ ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፡ እርሱም የዳዊት ሥር፡ መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ፥ ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ ድል ነሥቷል' አለ፡፤"* የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል፡ ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ተቀብለው፡ በምግባር ስለፈጸሙት፡ እውነተኞቹ እስራኤል፡ እነርሱ መኾናቸው ተረጋግጧል፡፡

ዘፍጥ. ፵፱፥ ፱-፲፤ ራእ. ፭፥ ፩-፭፡፡

| | |
|---|---|
| የየካቲት ወር ምንባብ፡ | ትንቢተ ዮናስና የዮሓንስ ወንጌል፡፡ |

# ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ወርኀ መጋቢት ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

1999 Era of Mercy. Month of Megabit (Mar.-Apr., 2007). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፴ 8<br>በዓለ ትንሣኤ ፋሲካ፤ | ማስታወሻ:- | | | | | ፩ 10<br>አጼ ዮሓንስ ፬ኛ: የመተማው ሰማዕት: በእስላም ወራሪ የተሰይፈ |
| ፪ 11<br>ደብረ ዘይት፤ | ፫ 12 | ፬ 13 | ፭ 14<br>ገብረ መንፈስ ቅዱስ | ፮ 15 | ፯ 16 | ፰ 17<br>ማትያስ: ከ02ቱ ሓዋርያት 1ዱ |
| ፱ 18<br>ገብር ኄር | ፲ 19 | ፲፩ 20<br>አባ አሌፍ: ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ | ፲፪ 21 | ፲፫ 22 | ፲፬ 23 | ፲፭ 24 |
| ፲፮ 25<br>ኒቆዲሞስ | ፲፯ 26 | ፲፰ 27 | ፲፱ 28 | ፳ 29 | ፳፩ 30 | ፳፪ 31 |
| ፳፫ 1<br>ሆሣዕና<br>ዳንኤል ነቢይ | ፳፬ 2<br>የሰሙነ ሕማማት መግቢያ፤<br>ንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክ | ፳፭ 3<br>የበጋ ወራት ማብቂያ | ፳፮ 4<br>የበልግ ወራት መግቢያ | ፳፯ 5<br>ጸሎተ ሓሙስ፤<br>አጼ ገላውዴዎስ: ካቶሊካውያንን የተቋቋመና በእስላም ወራሪ ሰማዕትነትን የተቀበለ፤<br>የጌታ የመጀመሪያ ስቅለቱ ቀን፤ | ፳፰ 6<br>ስቅለት፤<br>ቈስጠንጢኖስ ንጉሥ: ስለሃይማኖትና ስለፍትሓ ነገሥት ዝግጅት: የ3)08 ሊቃውንት ጉባኤን በኒቅያ ያሰባሰበ | ፳፱ 7<br>ጌታ በመቃብር ያረፈባት ቀዳሚት ሰንበት፤<br>የጌታ የመጀመሪያ ትንሣኤው ቀን |

*“እነሆ፥ ለዳዊት: ጻድቅ ቍጥቋጥ የማስነሣበት ዘመን ይመጣል:: እርሱም እንደንጉሥ ይነግሣል፤ ይከናወንለታልም፤ በምድርም: ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል:: ...በዘመኑ እውነት ታብባለች፤ ሰላምም ይበዛል:: ከባሕር እስከባሕር ድረስ፥ ከወንዝም እስከምድር ዳርቻ ድረስ ይገዛል:: በፊቱም ኢትዮጵያውያን ይሰግዳሉ:: ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ::”...“እግዚአብሔር ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው፤ በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ:: አንተ የእባቦችን ራስ: በውኃ ውስጥ ሰበርህ! የዘንዶውንም ራሶች ቀጠቀጥህ! ለኢትዮጵያ ሰዎችም ምግባቸውን ሰጠሃቸው!”* ኤር.፳፫፥ ፩-፭፤ መዝ.፸፩፥ ፯-፱፤ ፸፫፥ ፲፪-፲፬::

| | |
|---|---|
| የመጋቢት ወር ምንባብ: | አሪት ዘዳግም፥ ሰቆቃወ ኤርምያስ፥ የማርቆስ ወንጌል |

# ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ሚያዝያ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

1999 Era of Mercy. Month of Miazia (Apr.-May, 2007). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ቅዳሜ Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፩ ማዕዶት: (በሕይወተ ሥጋ እያሉ: በመንፈስ: ወደ ትንሣኤ ሕይወት መሻገር) 9 | ፪ 10 | ፫ 11 | ፬ 12 | ፭ 13 ሕዝቅኤል ነቢይ | ፮ 14 አርበኛው መሪ ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ |
| ፯ 15 ዳግም ትንሣኤ፤ ኢያቄም: የድንግል ማርያም አባት | ፰ 16 | ፱ 17 | ፲ 18 | ፲፩ 19 | ፲፪ 20 ደብረ ብርሃን በ05)@3 ዓ. ም በአሕመድ ግራኝ የተቃጠለበት | ፲፫ 21 በ09)@8 ዓ. ም. ፋሺስት ጣልያን ማኅበረ ሥላሴን: በአየር ኃይሉ የደበደበበት |
| ፲፬ 22 | ፲፭ 23 በ09)@8 ዓ. ም. 3 የማኅበረ ሥላሴ ገዳም መነኰሳት: በፋሺስት ጣልያን ጦር የተሠዉበት | ፲፮ 24 | ፲፯ 25 ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ከ02ቱ ሓዋርያት 1ዱ | ፲፰ 26 | ፲፱ 27 | ፳ 28 |
| ፳፩ 29 እጨጌ ዕንባቆም: ሰባኬ ሃይማኖትና ሓዋርያ | ፳፪ 30 | ፳፫ 1 ጊዮርጊስ ሰማዕት | ፳፬ 2 ርክበ ካህናት፤ | ፳፭ 3 | ፳፮ 4 | ፳፯ 5 ኢትዮጵያ: በፋሺስት ጣልያን ላይ በተቀዳጀ ችው ድል: ነጻነቷ የሚጠበቀው: በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ የተረጋገጠበት |
| ፳፰ 6 | ፳፱ 7 | ፴ 8 ማርቆስ ወንጌላዊ | ማስታወሻ:- | | | |

*የሳባ ንግሥት: በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን: የሰሎሞንን: ዝናውን በሰማች ጊዜ: ስለሃይማኖቱና ስለእውነ ተኛ ማንነቱ: በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ ከታላቅ ጓዝ ጋር ከአገርዋ ከኢትዮጵያ ተነሥታ: ወደኢየሩሳሌም መጣች:: ለንጉሡም: መቶ ሃያ መክሊተ ወርቅ፥ እጅግም ብዙ ሽቱ፥ የከበረም ዕንቍ ሰጠችው፤ የሳባ ንግ ሥት: የሰጠችውን የመሰለ የስጦታ ብዛት: ከዚያ ወዲያ አልመጣም:: የትንቢቱ ፍጻሜና ዘላለማዊው ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ: ከእርሱ ምልክትን ለሚጠይቅ: ከሃዲና ዓመፀኛ፥ ዘማዊም ትውልድ: እንዲህ የሚል: የመ ጨረሻ መልስን ሰጠ:- ንግሥተ ዓዜብ (ኢትዮጵያ): በፍርድ ቀን: ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፋረዳለች፥ ታሳፍረዋለችም፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት: ከምድር ዳር መጥታለችና፤ እነሆም: ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ! ከዚህ ፍርድ ለመዳን: እጆቿን ወደእግዚአብሔር ዘርግታ ከምትኖረው: ከኢትዮጵያ ጋር: የምድር መንግሥታት መሪዎች ኹሉ: ለእግዚአብሔር ተቀኙ! ዘምሩም!*

፩: ነገ. ፲፥፩-፲፤ ማቴ. ፲፪፥ ፴፪፤ መዝ. ፷፯፥፴፩-፴፪::

| የሚያዝያ ወር ምንባብ: | የጳውሎስ መልእክታት |
|---|---|

# ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ግንቦት ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

1999 Era of Mercy. Month of G'nbot (May-June, 2007). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | ፩ 9<br>ቅድስት ድንግል ማርያም በሊባኖስ ተራራ የመወለዷ መታሰቢያ | ፪ 10<br>ኢዮብ ጻድቅ: ኢትዮጵያዊ | ፫ 11 | ፬ 12 |
| ፭ 13<br>ኢትዮጵያውያኑ ኤርምያስ ነቢይ፥ ደቀ መዛሙርቱ አቤሜሌክ እና ባሮክ | ፮ 14<br>የደብረ ሊባኖሷ ቅድስት ሰሎሜ ኢትዮጵያዊት | ፯ 15 | ፰ 16<br>የመጀመሪያው የጌታ የዕርገት ቀን | ፱ 17<br>ዕርገት<br>ዕሌኒ ንግሥት: የጌታን መስቀል አስቆፍራ ያስገኘች | ፲ 18<br>አናንያ፥ አዛርያና ሚሳኤል: በሃይማኖታቸው ጽናት ከባቢሎን እሳት የዳኑት | ፲፩ 19<br>ያሬድ: ኢትዮጵያዊው ማኅሌታይ ካህን፤ አባ አሴር: የባሌ መምህር |
| ፲፪ 20<br>አጼ እስክንድር: የእስላምን ወራሪ ጦር ሲከላከል: ሰማዕትነትን: በወጣትነቱ የተቀበለ፤ ዮሓንስ አፈወርቅ | ፲፫ 21<br>የደብረ ሊባኖስ ገዳም መነኰሳት በ09)@9 ዓ. ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር የተሠዉበት | ፲፬ 22 | ፲፭ 23<br>ናትናኤል: ከ02ቱ ሓዋርያት 1ዱ | ፲፮ 24 | ፲፯ 25 | ፲፰ 26<br>መንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያ በሓዋርያት ላይ የወረደበት በዓለ ሃምሳ |
| ፲፱ 27<br>በዓለ መንፈስ ቅዱስ (በዓለ ሃምሳ)<br>ኢትዮጵያዊው አቡነ እግዚእ | ፳ 28<br>የጾመ ሓዋርያ መግቢያ፤ ቅዱስ አጼ ካሌብ: ወደናግራን (የመን) ግዛቱ: በመርከብ ዘምቶ: አይሁዳዊዉን ወራሪ ጠላት: ድል ያደረገው | ፳፩ 29<br>የደርግ የክህደት አገዛዝ በ09) * 3 ዓም የተወገደበት | ፳፪ 30<br>ጾመ ድኅነት:- የረቡዕና ዓርብ ጾም መነሻ | ፳፫ 31 | ፳፬ 1<br>ዕንባቆም ነቢይ | ፳፭ 2<br>ቅድስት ሰሎሜ: በሕፃኑ ኢየሱስና እናቱ ስደት ያልተለየች |
| ፳፮ 3<br>ቶማስ: ከ02ቱ ሓዋርያት 1ዱ | ፳፯ 4 | ፳፰ 5 | ፳፱ 6<br>አባ አፍጼ፤ አባ ጉባ: ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ቱ | ፴ 7 | ማስታወሻ:- | |

*ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደመቅደስ ወጥቶ ሲያስተምር: ሊገድሉት ለሚፈልጉት አይሁድ: "ቅን ፍርድን ፍረዱ እንጂ: መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!" አላቸው:: ለምን እንዲህ አላቸው? "መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!" የሚለው የጌታ ቃል: ቀድሞ: በሙሴ ላይ የተነሣሣባቸው ቅንዓት የተከሠተው: በኢትዮጵያዊት ሚስቱ ምክንያት እንደነበረ ኹሉ: አሁን ደግሞ በእርሱ: በኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊነት ላይ የተቀጣጠለ መኾኑን ሲያመለክታቸው እንደኾነ ማስተዋል ነው:: "'የእስራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ: ለእኔ: እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?' ይላል እግዚአብሔር" ሲል: ነቢዩ አሞጽ የተናገራቸውን ቃል: በዚያን ጊዜም አላስተዋሉ ትም::* ዮሓ ፯፥ ፲፬-፳፬፤ ዘኍል. ፲፪፥ ፩-፲፮፤ አሞ. ፱፥ ፯::

| የግንቦት ወር ምንባብ: | መጻሕፍተ አስቴር፥ ምሳሌና መክብብ |
|---|---|

# ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ሰኔ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

1999 Era of Mercy. Month of Seney (June-July, 2007). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ቅዳሜ Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | | ፩ 8 ወንድሞቹ የሸጡት የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ እና ካማዊት ሚስቱ አስናት | ፪ 9 |
| ፫ 10 | ፬ 11 | ፭ 12 | ፮ 13 በፋሺስት ጣልያን የተመራ የራያ እስላም፡ በ09)@9 ዓ. ም. የሸዋ ቆላ ኢትዮጵያዎችን በሰለባ የፈጀበት | ፯ 14 | ፰ 15 | ፱ 16 ሳሙኤል ነቢይ |
| ፲ 17 | ፲፩ 18 | ፲፪ 19 ሚካኤል ሊቀ መላእክት፤ አጼ ላል ይበላል | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22 | ፲፮ 23 |
| ፲፯ 24 አባ ገሪማ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ | ፲፰ 25 | ፲፱ 26 | ፳ 27 ሕንጻታ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ቤተ ክርስቲያን መታነጽ የተጀመረበት፤ ኤልሳዕ ነቢይ | ፳፩ 28 በቅዱሱ ኪዳን ላይ ክህደትና ዓመፅ የፈ ጸመውን ትውልድ ሊቀጣ የተላከው ግፈኛው ደርግ በ09)^6 ዓ. ም. ተቋቋመ | ፳፪ 29 | ፳፫ 30 ንጉሥ ሰሎሞን የምኒልክ አባት |
| ፳፬ 1 ኢትዮጵያዊው ሙሴ (ጸሊም) | ፳፭ 2 ሓዋርያው ይሁዳ፡ የጌታ የቅርብ ዘመድ፤ የበልግ ወራት ማብቂያ | ፳፮ 3 ኢያሱ ወልደ ነዌ፤ የክረምት ወራት መግቢያ | ፳፯ 4 | ፳፰ 5 | ፳፱ 6 በሺ፬፻፬ ዓ.ም. የተቀባው ስመ ጥሩው ጻድቅ ቀዳማዊ አጼ ቴዎድሮስ | ፴ 7 የላስታ ላልይበላል (ላሊበላ) አብያተ ክርስቲያን፡ በ05 )"5 ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ጦር የተበዘበዙበት |

*“የእግዚአብሔር መልአክ፡ ፊልጶስን፡- 'ተነሥተህ በደቡብ በኩል፡ ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው፡ የምድረ በዳ መንገድ ኺድ!' አለው:: ተነሥቶም ኼደ:: እነሆም፡ ሕንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ፥ በገንዘቡዋም ኹሉ የሠለጠነ፡ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር:: ሲመለስም፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ፊልጶስን፡ 'ወደዚህ ሠረገላ ቀረብና ተገናኝ!' አለው:: የአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ የኾነው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም፡ ወዲያው፡ 'ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ!' ስላለ፡ አጠመቀው:: ከውኃው ከወጡ በኋላ፡ አቤሜሌክ፡ በተደረገለት ዕፁብ ድንቅ መለኮታዊ የቸርነት ሥራ፥ በተቀዳጀውም ዘለዓለማዊ የመንፈስ ቅዱስ ብፅዕና፡ እጅግ ተደንቆና ደስ ብሎት ስለነበረ፡ ፊልጶስ፡ ካጠገቡ፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመነጠቁን ተአምር ሳያስተውል፡ ዝም ብሎ፡ የሠረገላ መንገዱን ቀጠለ::*

የሐዋ. ፰፥ ፳፮-፵::

| የሰኔ ወር ምንባብ፡ | ተረፈ ኤርምያስ፥ የሓዋርያት ሥራና መልእክታት |
|---|---|

# ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ሐምሌ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

1999 Era of Mercy. Month of Hamley (July-Aug., 2007). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 8 | ፪ 9<br>ታዴዎስ፡ ከ02ቱ ሓዋርያት 1ዱ | ፫ 10 | ፬ 11 | ፭ 12<br>የጾመ ሓዋርያት ማብቂያ፤<br>ቅዱሳን ሓዋርያት ጴጥሮስ ወጳውሎስ | ፮ 13<br>ዕርገተ እዝራ | ፯ 14<br>ሥሉስ ቅዱስ፡ በአብርሃም ቤት የተገኙበት፤<br>በ09)@9 ዓ. ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር በሰማዕትነት የተሠዉት "5ቱ የደብረ ሊባኖስ መነኵሳት |
| ፰ 15 | ፱ 16 | ፲ 17 | ፲፩ 18 | ፲፪ 19 | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 |
| ፲፭ 22<br>ኤፍሬም ሶርያዊ የውዳሴ ማርያም ደራሲ | ፲፮ 23 | ፲፯ 24<br>እጨጌ እንድርያስ፡ በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የነበረ፤<br>ነቢዩ ዮናስ ነነዌ የገባበት | ፲፰ 25<br>ያዕቆብ፡ የጌታ የቅርብ ዘመ ድና በኢየሩሳሌም የመጀመሪያው ሓዋርያ፤<br>ኢትዮጵያውያኑ ጦብያና ጦቢት | ፲፱ 26<br>ሊቀ መላእክት ገብርኤል፡ ቂርቆስን እና እናቱ ኢየሉጣን ከሚነድድባቸው እሳት ያዳነበት | ፳ 27 | ፳፩ 28<br>አጼ ሠርፀ ድንግል፡ ሃይማኖታዊው ተጋዳይ |
| ፳፪ 29<br>ዑራኤል ሊቀ መላእክት | ፳፫ 30<br>በ09)@8 ዓ. ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር የተሠዋው ኢትዮጵያዊው ሰማዕት አባ ጴጥሮስ | ፳፬ 31<br>የደብረ ሊባኖስ ገዳ ም በ05)"3 ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ የተቃጠለበት፡ መነ ኮሳቱም ራሳቸውን በእሳቱ የማገዱበት | ፳፭ 1<br>አባ ሕፃን ሞአ ኢትዮጵያዊ | ፳፮ 2<br>ጻድቅ ዮሴፍ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ሕፃኑ ኢየሱስንና እናቱን፡ ለማገልገል በፈጣሪ የተመረጠ | ፳፯ 3 | ፳፰ 4 |
| ፳፱ 5 | ፴ 6<br>ማርያም ክብራ፡ (እቴጌ ናዖድ ሞገሳ) የአጼ ናዖድ ሚስት | ማስታወሻ፡- | | | | |

*እንግዴህ አይሁድ፡ "ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ!" ስላለ፡ ስለኢየሱስ አንጐራጐሩ፤ "ይህ ሰው፡ ሥጋውን ልንበላ፥ ደሙንም ልንጠጣ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል?" ብለውም ተከራከሩ። ከዚህ የተነሣ፡ ከደቀ መዛሙርቱ ሳይቀር፡ "ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል?" ብለው ብዙዎቹ ወደኋላቸው ተመለሱ።* በዚህ ጊዜ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *"እውነት፥ እውነት እላችኋለሁ! ሥጋዬን ካልበላችሁ፥ ደሜንም ካልጠጣችሁ፡ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፤ ሥጋዬን የሚበላ፥ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ እኔም፡ በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።"* ሲል፡ ሊድን ለሚፈልግ፡ ለዓለሙ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ የመጨረሻ አዋጅ የኾነውን የእግዚአብሔርን እውነት ገልጦና አስረግጦ ተናገረ። ዮሐ.፮÷ ፶፩-፶፱።

| የሓምሌ ወር ምንባብ፡ | መጽሓፈ ሲራክ፥ መጽሓፈ ጥበብ። |
|---|---|

# ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ነሐሴ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

1999 Era of Mercy. Month of Nehassey (Aug.-Sept., 2007). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | ፩ የፍልሰታ 7<br>ለማርያም ጾምና ሱባዔ መግቢያ፣ ጌታን የገነዙት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ | ፪ 8 | ፫ 9 | ፬ 10 | ፭ 11<br>አባ ፊልጶስ ዘደብረ ቢዘን |
| ፮ 12<br>ማርያም መግደላዊት: የጌታን ትንሣኤ አይታ ያበሠረች | ፯ 13<br>አጼ ናዖድ: የመልክዓ ማርያም እና መልክዓ ኢየሱስ ደራሲ | ፰ 14 | ፱ 15 | ፲ 16 | ፲፩ 17 | ፲፪ 18 |
| ፲፫ 19<br>ጌታ በግርማ መለኮቱ የታየበት ደብረ ታቦር (ቡሔ) | ፲፬ 20 | ፲፭ 21<br>የፍልሰታ ለማርያም ጾምና ሱባዔ ማብቂያ፣ | ፲፮ 22<br>የቅድስት ድንግል ማርያም በዓለ ትንሣኤ | ፲፯ 23 | ፲፰ 24<br>አዝማች አዳሉ: የአሕመድ ግራኝንወረራ በጀግንነት ተቋቁሞ የተሠዋ | ፲፱ 25 |
| ፳ 26 | ፳፩ 27 | ፳፪ 28 | ፳፫ 29<br>አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ: ኢትዮጵያዊ: የመዓዛ ቅዳሴና የሰዓታት ጸሎታት ደራሲ | ፳፬ 30<br>በ02ኛው ) ዓመት የኢትዮጵያን ሥር ዓተ መንግሥት ያስከበረ: እጨጌ ተክለ ሃይማኖት፣ ክርስቶስ ሠምራ ኢትዮጵያዊት | ፳፭ 31 | ፳፮ 1 |
| ፳፯ 2<br>እጨጌ ፊልጶስ፣ ታላቁ ሓዋርያና አጼ ዓምደ ጽዮን: ንስሓ እንዲገባ በግልጽ በመገሠጹ ጽኑ መከራን የተቀበለ | ፳፰ 3<br>አብርሃም÷ ይስሓቅና ያዕቆብ | ፳፱ 4<br>ንዋየ ክርስቶስ (አለቃ ዘካርያስ) እስላሞችን: በሃይማኖት ጉባኤ የረታና ብዙዎቹን ወደክርስትና የመ ለሰ ኢትዮጵያዊ ሓዋርያ÷ የኢትዮ ጵያዊነት አብነት ድልድይና ባለአደራ | ፴ 5<br>መልከ ጼዴቅ: ቅዱሱን ኪዳን: ከኖኅ የተረከበና አብርሃምን የባረከ ኢትዮጵያዊ÷ የኢየሱስ ክርስቶስ ተቀዳሚ አርአያ | | | |

## ጳጉሜ

| ሓሙስ | ዓርብ | ቅዳሜ | እሑድ | ሰኞ | ማግ ሰኞ |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 6<br>የንስሓ ጾም መግቢያ | ፪ 7 | ፫ 8<br>ሩፋኤል ሊቀ መ ላእክት፣ አጼ ዘ ርዓ ያዕ ቆብ | ፬ 9<br>የቅዱሳን ኹሉ መታሰቢያ | ፭ 10<br>የንስሓ ጾም ማብቂያ ዓሞጽ ነቢይ | ፮ 11 |

*መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል: ድንግል ማርያምን: "ደስ ይበልሽ! ጸጋ የሞላብሽ ሆይ! እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው! አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ!" አላት:: መንፈስ ቅዱስ የሞላባት ኤልሣቤጥም: "አንቺ: ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ! የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው!" አለች::*

*ቅድስት ድንግልም: "ነፍሴ: እግዚአብሔርን: እጅግ ታልቀዋለች፣ መንፈሴም: በአምላኬና በመድኃኒቴ: ሐሤት ታደርጋለች፣ የባሪያውን መከራዋን ተመልክቷልና:: እነሆ: ከዛሬ ጀምሮ: ትውልድ ኹሉ: 'ብፅዕት' ይሉኛል፣ ብርቱ የኾነ እርሱ: በእኔ: ታላቅ ሥራን አድርጓልና!" አለች:: ሉቃ. ፩÷ ፳፯-፶::*

| የነሓሴና የጳጒሜ ወር ምንባብ: | የሉቃስ ወንጌል÷ መጽሓፈ ኢዮብ÷ መጽሓፈ ጦቢትና ራእየ ዮሓንስ |
|---|---|